የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 43
ADDIS ABABA 23 July, 2007


<u>ማ ው ጫ</u>


አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፯/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

ከቤልጂየም-ሉክሰምበርግ ኢኮኖሚክ ዩኒየን ጋር ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ …. ገጽ ፫ሺ፮፻፸፱


<u>**CONTENTS**</u>


**Proclamation No. 537/2007**

The Belgian-Luxembourg Economic Union Agreement on the Reciprocal Promotion and Protection of Investment Ratification Proclamation …. Page 3679


## አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፯/፲፱፻፺፱

## ከቤልጂየም-ሉክሰምበርግ ኢኮኖሚክ ዩኒየን ጋር ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት <u>ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በቤልጂየም-ሉክሰምበርግ ኢኮኖሚክ ዩኒየን መካከል ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋት እና ዋስትና ለመስጠት ጥቅምት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ስምምነት በብራስልስ የተፈረመ ስለሆነ፤

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋዮቹ ሀገሮች ህጎች መሠረት መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ ስለተገለጸ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 537/2007.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON THE RECIPROCAL PROMOTION AND PROTECTION OF INVESTMENT WITH THE BELGIAN-LUXEMBOURG ECONOMIC UNION

**WHEREAS,** the Agreement, on the reciprocal Promotion and Protection of Investment between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Belgian-Luxembourg Economic Union is signed in Brussels on the 26th day of October 2006;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that it shall enter into force on the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channel;

**WHEREAS,** the House of People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on 21st day of June, 2007;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ከቤልጂየም-ሉክሰምበርግ ኢኮኖሚክ ዩኒየን ጋር ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፯/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በቤልጅየም-ሉክሰምበርግ ኢኮኖሚክ ዩኒየን መካከል ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት በብራስልስ ከተማ፣ ጥቅምት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. <u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ኃላፊነት</u>

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Belgian-Luxembourg Economic Union Agreement on the Reciprocal Promotion and Protection of Investment Ratification Proclamation No.537/2007."

## 2. Ratification of the Agreement

The Reciprocal Promotion and Protection Investment Agreement Signed in Brussels on the 26th day of October 2006, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Belgian-Luxembourg Economic Union is ratified.

## 3. Power of the Ethiopian Investment Agency

The Ethiopian Investment Agency is hereby empowered to implement this Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 23 day of July, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**